DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች፡ ለመጀመሪያ ደረጃ (Elementary) ተማሪዎች፣ የተርም (Term) 2፣ የመማሪያ ሞዴሎች የምርጫ ሂደቶች

DCPS፣ ለPK3-5ተኛ ክፍሎች ውስጥ ላሉ ለመጀመሪያ ደረጃ (elementary) ተማሪዎች ወደ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር እየተመለሰ ባለበት ግዜ፣ የተማሪ እና የሠራተኛ ደህንነት መጠበቁን ለማረጋገጥ ሲባል፣ ቦታዎቹ የተወሰኑ ይሆናሉ። DCPS፣ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በሙሉ ቦታ ማግኘታቸውን ዋስትና መስጠት ስለማይችል፣ በዘፈቀደ አሰራር (randomized) የምርጫ ሂደቱን ተጠቅመን፣ በአኩልነት ቦታዎችን እናከፋፍላለን። ይህ ሰነድ፣ ስለ እዚህ ሂደት ለወላጆች መረጃ ይሰጣል። በተርም (Term) 2 ምን መጠበቅ እንዳለባችሁ፣ ሁሉን አቀፍ የሆነውን መረጃ፤ እባክዎን በ[ https://dcpsreopenstrong.com/schedule/term2/] ይጎብኙ።

**በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር እና በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜው መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?**

ከተርም (Term) 2 ጀምሮ፣ በመጀመሪያ ደረጃ (elementary) ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች፣ DCPS ሁለት ዓይነቶች በአካል ተገኝቶ (in-person) ፕሮግራሞችን ይሰጣል፡ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር እና የእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች።

- **በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር** ተማሪዎች በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ሆነው፤ ከክፍል ውስጥ አስተማሪ ጋር፣ በትምህርት ቤቶቻቸው ውስጥ በቀጥታ (live)፣ በሣምንት አምስት ቀናትን በአካል ተገኝቶ የትምህርት አሰጣጥን ሲያገኙ፤ እሮብ እሮብ፣ ደግሞ በግማሽ ቀን ለመማር ሲመደቡ ነው። የየዕለቱ የጊዜ ሰሌዳ፣ በመደበኛ የትምህርት ቀን ከሚደረገው ጋር ተመሣሣይ ይሆናል። ከPK3-5 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ፣ ለመጀመሪያ ደረጃ (elementary) ተማሪዎች፣ በተርም (Term) 2 ውስጥ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር፤ ሰኞ፣ ጥቅምት 30 (November 9) ይጀምራል።
    - ለልዩ ትምህርት (special education) ተማሪዎች፣ በልዩ የትምህርት ክፍል ውስጥ የተዘጋጀ (self-contained) በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር: በልዩ የትምህርት ክፍል ውስጥ የተዘጋጀ (self-contained) ውስጥ፣ የልዩ ትምህርት (special education) ፕሮግራም ተማሪዎች፣ ከPK3-5ተኛ ክፍሎች ውስጥ ባሉ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማሪያ በሆኑ፣ ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ውስጥ እና በሁሉም በ'River Terrace' ክፍሎች ውስጥ ገብተው ለመማር ቦታ እንዲያገኙም ብቁ ያደርጋቸዋል።

- **የእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች**: ተማሪዎች በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ሆነው በክፍል ውስጥ እንክብካቤ ከሚሰጥ አዋቂ ጋር በመሆን፣ ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) መማርን ለሁሉም ተማሪዎች፣ በሣምንት አምስት ቀናት፤ እሮብ እሮብ፣ በግማሽ ቀን ሲመደቡ ነው። ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ፕሮግራምን ማካሄድ በሚቀጥሉበት ጊዜ፣ ከእኩዮቻቸው ጋር ማህበራዊነትን (socialize) የማድረግ ዕድል ይኖራቸዋል። የእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች፣ በPK3፣ PK4፣ በመዋዕለ ሕፃናት (Kindergarten) እና በ1ኛ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ለተማሪዎች፤ በህዳር 7 (November 16) ሣምንት ውስጥ ይጀምራሉ። የእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች፣ በ2ተኛ፣ 3ተኛ፣ 4ተኛ እና 5ተኛ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ለተማሪዎች፤ በህዳር 21 (November 30) ሣምንት ውስጥ ይጀምራሉ።

በእነዚህ ሞጁሎች (models) ላይ ተጨማሪ መረጃን ከፈለጉ፣ እባክዎን በ[ https://dcpsreopenstrong.com/schedule/term2/] ይጎብኙ።

**ከ6ተኛ እስከ 12ተኛ ክፍሎች ውስጥ በአካል ተገኝቶ (in-person) ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ በተርም (Term 2) ውስጥ ብቁ ይሆናሉ?**

የለም፤ ተማሪዎቹ በ'ተማሪ እርዳታ ማዕከሎች (Student Support Centers) ውስጥ ካልተካፈሉ በስተቀር፤ ከ6ተኛ – 12ተኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ (secondary) ተማሪዎች፣ ለተርም (Term) 2፣ (Nov.9 – Jan. 29) ባለው ጊዜ፣ ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ሆነው እንዲቀጥሉ ይደረጋል። በተማሪ እርዳታ ማዕከሎች (Student Support Centers) ላይ ተጨማሪ መረጃን ከፈለጉ፣ እባክዎን በ[ https://dcpsreopenstrong.com/schedule/student-support-centers/] ይጎብኙ። ከ6ተኛ እስከ 8ተኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶችን በ'River Terrace Education Center' ውስጥ፣ በበለጠ ጠንከር

ባለ ሁኔታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ብቻ እንዲመጡ የሚጠበቁ ሲሆን፣ በተርም (Term) 2 ውስጥም በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማርም ብቁዎች ያደርጋቸዋል።

**ተማሪዬን ወደ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ወይም በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ውስጥ ለመላክ እፈልጋለሁ። ማመልከት አለብኝ?**

የለም፣ ቤተሰቦች ሁኔታው እንዲታይላቸው፣ ማመልከቻን መሙላት ወይም ሌላ ማንኛውንም እርምጃን መውሰድ አያስፈልጋቸውም። ሁሉም ተማሪዎች እንደተካተቱ ለማረጋገጥ፣ DCPS፣ ሁሉም ቤተሰቦች ቦታውን ለማግኘት ፍላጎት እንዳላቸው በመገመት፤ ቦታው የተሰጣቸው ቤተሰቦች፣ ቦታቸውን የመውሰድ ወይም ያለመውሰድ ዕድል፤ አማራጮቹ እስካሉላቸው ድረስ መምረጥ እንዲችሉ ያደርጋል።

**ተማሪዬን ወደ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር መላክ ፍላጎት የለኝም። ተማሪዬን ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ትምህርት አሰጣጥ ማግኘቱን እንዲቀጥል ለማድረግ፤ የማደርገው ነገር አለ?**

የለም! ሁሉም ቤተሰቦች፣ ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ሆነው የመቆየት አማራጭ አላቸው። ተማሪዎ ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ትምህርት አሰጣጥ ማግኘቱን እንዲቀጥል መውሰድ የሚገባዎ ማንኛውም ነገር አይኖርም። በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ወይም በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ለመማር ቦታ ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል፣ እና፤ ይህ በሚሆን ጊዜ፣ የተሰጠውን ቦታ ላለመውሰድ (decline ለማድረግ) መፈለግዎን፤ ቦታው ለሌላ ተማሪ መሰጠጥ እንዲችል፣ ለትምህርት ቤቱ ምላሽ በመስጠት እና ማሳወቅ ይኖርብዎታል ወይም በdcps.planning@k12.dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

**ቦታውን ከተቀበልኩኝ በኋላ፣ ሃሳቤን ቆይቼ መቀየር እችላለሁ?**

አዎን፣ በፈለጉት በማንኛውም ጊዜ ተማሪዎን(ዎችዎን) ከአካል ተገኝቶ (in-person) ፕሮግራም አሰጣጥ፣ ወደ መኖሪያ ቤት ውስጥ መማር እንዲዛወር/ሩ፣ ትምህርት ቤትዎን በማሳወቅ ማዘዋወር ይችላሉ። ተማሪው ወደ መኖሪያ ቤት ውስጥ መማር ከተዛወረ በኋላ፣ በአሁኑ ተርም (term) ጊዜ ውስጥ እንደገና ወደ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ወይም በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ለመመለስ አይችሉም።

**በአንድ ዓይነት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ወንድምና እህታማቾችን፣ አብረው ወደ እንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ወይም በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር እንዲገቡ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ፣ DCPS ምን እርምጃን ይወስዳል?**

DCPS፣ የወንድምና እህታማቾች (siblings) በትምህርት ቤት ውስጥ አብረው መሆናቸው ለቤተሰቦች ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ስለሚያውቅ፤ በአንድ ዓይነት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩን ወንድምና እህታማቾችን በአንድ ዓይነት የጊዜ ሰሌዳ ለመመደብ ጥረት ያደርጋል። ይህን ግቡን ለማገዝ፣ በተቻለ ሁኔታ፣ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ወንድምና እህታማቾችን (siblings) ለይቶ፣ በአንድ ዓይነት የጊዜ ሰሌዳ ለመመደብ ተመራጭ እንዲሆን፣ DCPS ከትምህርት ቤቶቹ ጋር ይሠራል። ሆኖም፣ በቤተሰቡ ውስጥ ያሉ ሁሉም ወንድምና እህታማቾች (siblings)፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ወይም በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ውስጥ በአንድነት ቦታ እንደሚያገኙ፣ DCPS ዋስትና አይሰጥም።

**DCPS፣ 'ወንድምና እህታማቾች' (siblings) የሚለውን እንዴት ነው የሚተረጉመው?**

DCPS፣ ወንድምና እህታማቾች (sibling) ለሚለው ትርጓሜ ሲሰጥ፤ ልጁ ቢያንስ አንዱ ወላጅ ወይም ሕጋዊ አሳዳጊው ባለበት በመደበኛነት በአሁኑ ጊዜ የDCPS ተማሪ እና ነዋሪ ሆነው፤ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖር ተማሪ ነው (*5-E DCMR § 2199.2*)። ይህ ትርጓሜ፤ DCPS፣ ለ'My School DC' ሎተሪ ማከናወኛነት ከተጠቀመው ጋር አንድ ዓይነት ነው። DCPS የወንድምና እህታማቾች (sibling) በአንድ ቦታ ማዛመድ ሁኔታን የሚያከናውነው፣ እስከ መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም (October 5, 2020) ድረስ በአንድ ዓይነት ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ ብቻ ቅድሚያ በመስጠት ነው።

**ሠራተኞች ያላቸውን፣ የልጅ እንክብካቤን (childcare) ፍላጎቶችን በዚህ የተማሪ ምርጫ ሂደት ወቅት፣ DCPS አስተያየት ያደርግበታል?**

አዎን። አብዛኛዎቹ ሠራተኞቻችን የልጅ እንክብካቤ (childcare) አግኝተው፣ በአካል (in-person) ወደስራቸው ሪፖርት የማድረግ ፈታኝ ሁኔታ እንደሚገጥማቸው፣ DCPS ይገነዘባል። በዚህም ምክንያት፣ በሁለቱም፤ በአንደኛ ደረጃ (elementary) ትምህርት ቤቶች እና በትምህርት ካምፓሶች (education campuses) በተርም (Term) 2፣ እና ከPK እስከ 5ተኛ ክፍል፤ በመስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም (October 5,

2020) በDCPS ውስጥ የተመዘገበ ተማሪ ላላቸው ሠራተኞች በሙሉ፤ ከPK እስከ 5ተኛ ክፍል ውስጥ ያላቸው ተማሪ(ዎች)፣ በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ውስጥ ቦታ ማግኘታቸው ዋስትና ይሠጠዋል።

## በአካል ተገኝቶ (in-person) የመማሪያ ክፍሎች

**በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር ቦታ ለማግኘት ማን ብቁ ይሆናል?**

እስከ መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም (October 5, 2020) ድረስ የተመዘገቡ ሁሉም ተማሪዎች፣ ቦታ ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ። DCPS በአካል ተገኝቶ (in-person) የመማሪያ ቦታዎች፣ ለተማሪዎች ከዕድልነት ባሻገረ ሁኔታ ቅድሚያ ለመስጠት በትጋት ይሠራል። ስለሆነም፤ በሚከተሉት ምድቦች ውስጥ የሚካተቱ ተማሪዎች፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) የመማሪያ ቦታዎችን ለማግኘት ተመራጭነትን ያገኛሉ።

- የቤት-አልባነት (homelessness) የገጠማቸው ተማሪዎች
- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና የግል የትምህርት ዕቅድ (Individualized Educational Plans (IEPs)፣ ያላቸው ተማሪዎች
- በአደጋ ላይ (at-risk) ተብለው የተለዩ ተማሪዎች (ይህ፤ በማደጎ እንክብካቤ ዘዴ ውስጥ ያሉ፣ እና TANF ወይም SNAP ለማግኘት ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን ይጨምራል)።

በተጨማሪም፣ ሂደቱ ለወንድም እና እህታማቾች (siblings) አማራጭን ይሰጣል። ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት የቡድን አባላቶች ውስጥ የሚገኙ ወንድምና እህታማቾች (siblings)፣ በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ ሊካተቱ ከማይችሉት ወንድምና እህታማቾች (siblings)፤ በበለጠ ሁኔታ ቅድሚያ ያገኛሉ።

**የብቁነቱ አሠራሩ፣ ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ውስጥ፣ የልዩ ትምህርት (special education) ክፍሎች ውስጥ ላሉትም፣ በአንድ ዓይነት ሁኔታ ነው የሚሠራው?**

በልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሙሉ፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) ቦታን ለማግኘት ሁሉም ብቁ ናቸው። ቦታዎቹ የሚሰጡት፣ በአገልግሎት ሰጪ ሠራተኛ መገኘትና አለመገኘት ላይ መሠረት አድርጎ ይሆናል። በልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ውስጥ ያሉ የቤት አልባነትን (homelessness) ተሞክሮ የገጠማቸው ተማሪዎች፣ ከሌሎች በልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ውስጥ ካሉ ሁሉ በበለጠ ሁኔታ የቦታ ማግኘት ምርጫ ይሰጣቸዋል። የ'River Terrace Education Campus'፣ በልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ውስጥ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ የልዩ ትምህርት (special education) ፕሮግራም ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት፣ በ'River Terrace' በሁሉም ክፍሎቹ ውስጥ በስራ ላይ ይውላል።

**ተማሪው በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ቦታን ለማግኘት፣ ተቀዳሚ የሆነውን መመዘኛ ማሟላቱን እንዴት ነው DCPS የሚለየው?**

DCPS፣ ስለ ምዝገባ ሁኔታ እና ስለ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ሁኔታ ለማረጋገጥ፣ ውስጣዊ የመረጃ ስብስቦችን (internal databases) ሊያመሳክር ይችላል። DCPS፣ ስለ መኖሪያ ቤት፣ ልዩ ትምህርት (special education) እና በአደጋ ላይ (at-risk) ያሉ ሁኔታቸውን ለማረጋገጥ፣ የስቴቱ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent for Education (OSSE)፣ ያለውን መረጃ (data) ሊጠቀም ይችላል።

**ተማሪዎችን በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ውስጥ የቦታ ምርጫ ለማድረግ፣ ትምህርት ቤቱ በራስ የመወሰን መብት ይኖረዋል?**

የትምህርት ቤት መሪዎች፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር፤ በአንድ ክፍል ውስጥ ከሁለት ቦታዎች ባልበለጠ የምርጫ ጥቆማዎችን የመስጠት አማራጭ ይሰጣቸዋል። ከላይ ካሉት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቡድኖች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብቻ፣ ለትምህርት ቤት ደረጃ (school-level) ምርጫ ብቁ ይሆናል። የትምህርት ቤት አመራሮች፣ ለመምረጥ አስተያየት መስጫ እውነታዎችን እና እንዴት አስተያየቶችን መስጠት እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጣቸዋል። ሁሉም የምርጫ አስተያየቶች፣ በDCPS ማዕከላዊ ቢሮ፣ ይታይ እና እንዲፈቀድ ይደረጋል። የትምህርት ቤት አመራሮች፣ አስተያየቶችን ለማስገባት ግዴታ የለባቸውም።

**ተማሪዬ በአካል ተገኝቶ (in-person) የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ቦታ ካገኘ፣ መቼ እና እንዴት አውቃለሁ?**

ቦታውን ካገኙ፣ ቤተሠቦች ይህንኑ ማስታወቂያ፤ እስከ ጥቅምት 13 (October 23) ድረስ ባለው ጊዜ ኢሜል የሚያገኙ እና ኢሜሉትን ተከትሎ ከትምህርት ቤቱ የስልክ ጥሪ ያገኛሉ። ውጤቶቹ ከተገለጹ በኋላ፣ ቤተሠቦች ወደ ትምህርት ቤቶቻቸውም መደወል ይችላሉ፣ ወይም በdcps.planning@k12.dc.gov ኢሜል በማድረግ፣ ስለሁኔታቸው ማረጋገጫ ማግኘት ይችላሉ።

ማዛመዱ በተከናወነበት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ውስጥ፣ ትምህርት ቤቱ ለሁሉም የተዛመዱ ቤተሰቦች የስልክ ጥሪ ያደርጋል። አንድ ጊዜ ትምህርት ቤቱ ከወላጅ ጋር ከተነጋገረ በኋላ፣ ቦታቸውን ለማረጋገጥ፣ ቤተሰቦች እስከ ሁለት የትምህርት ቀናት ይኖራቸዋል። በዚያ የጊዜ ገደብ ቤተሰቡ ምላሽ ካልሰጠ፣ የተሰጣቸውን ቦታ በማጣት፣ ተማሪዎቻቸው በመኖሪያ ቤት መማርን ይቀጥላሉ። ትምህርት ቤቱ ቤተሰቡን ማግኘት ካልቻለ፣ ሙከራውን ይቀጥላ፤ ሆኖም ቦታው ከ5 የትምህርት ቀናት በላይ፣ ምላሽ በማጣት ተይዞ ሊቆይ አይችልም።

**ልጄ በትምህርት ቤቴ ውስጥ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ክፍለጊዜዎች ቦታ አግኝቶ ከተዛመደ፣ ቦታውን እንዴት መቀበል እችላለሁ?**

በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር ቦታ ከተዛመዳችሁ፣ ቦታውን ወዲያውኑ መቀበላችሁን ማሳወቅ አለባችሁ። ቦታውን ለመቀበላችሁ ለማሳወቅ፣ ወደ ትምህርት ቤቱ በመደወልና ቦታውን እንደምትፈልጉት ማረጋገጥን ይጠይቃል። ከትምህርት ቤቱ ጋር የተደረገ ምንም ዓይነት ግንኙነት ከሌለ፣ ማዛመዱ ከተገለጸበት ቀን በኋላ ባለው አምስት የትምህርት ቀናት ውስጥ የቦታው የጊዜ ገደብ ያበቃል። በግል የትምህርት ዕቅዳቸው (Individualized Education Plans) ውስጥ፣ ለተማሪው መጓጓዣ አገልግሎት ላላቸው ተማሪዎች፣ ጥያቄውን ለማስገባት እንዲረዳው፣ የትምህርት ቤት ሠራተኛው ስለ መጓጓዣ ፍላጎቶቹ ይጠይቃል።

በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር ቦታውን ሲቀበሉ፣ ምናልባት የልጅዎ አስተማሪ ሊቀየር የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ሙሉ ለሙሉ ምናባዊ (all-virtual) በሆነ የጊዜ ሰሌዳ ላይ የሚቆዩ ተማሪዎች፣ አብዛኛውን ጊዜ፣ ከአንድ ዓይነት አስተማሪዎቻቸው ጋር ይቆያሉ። ሆኖም፣ ሙሉ ለሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ውስጥም፣ አንዳንድ የተማሪ-አስተማሪ ምደባ ለውጦች ሊኖሩ ይችላሉ።

**ልጄ በትምህርት ቤቴ ውስጥ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ክፍለጊዜዎች ቦታ አግኝቶ ከተዛመደ፣ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ትምህርት ላይ እንዲቀጥል ከመረጥኩኝ፣ ቦታውን ላለመቀበል ምን ማድረግ አለብኝ?**

ማንም ቤተሠብ፤ በአካል ተገኝቶ (in-person) በሚደረግ የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ መሳተፍ አያስፈልገውም። ሁሉም ቤተሰቦች፣ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መማርን የመቀጠል አማራጭ አላቸው። በአካል ተገኝቶ (in-person) መማሪያ ውስጥ፣ ቦታ ተሰጥቶዎት ከተዛመዱ፣ እና መቀበል ካልፈለጉ፤ እባክዎን በተቻለ ፍጥነት ወደ ትምህርት ቤትዎ ደውለው በማሳወቅ፣ ይህ ቦታ ለሚቀጥለው በተጠባባቂው ዝርዝር ውስጥ ላለ ባለተረኛ እንዲሰጥ ያድርጉ።

**የልጅዎን በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ቦታን ለመቀበል የተሰጠው የጊዜ ገደብ ቢያልፍብኝ ምን ይሆናል?**

በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር ቦታ ካገኙ፣ እና ቦታውን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቀበል ካልቻሉ፣ ያገኙትን ቦታ ያጣሉ። እንዲሁም፤ ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ቦታ ካገኙ እና ትምህርት ቤቱ የጊዜ ገደብ አድርጎ ያስቀመጠው የማብቂያ ቀን ካመለጠዎ፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር የተሰጠዎትን ቦታ ያጣሉ። የተሰጠዎትን ቦታ የጊዜ ገደቡ ከማብቃቱ በፊት፣ ለመቀበል እንደማይችሉ ካሰቡ፣ ወዲያውኑ ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ።

**በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ቦታን ተቀብዬ ነበር፤ ነገር ግን፣ ተማሪዬ በመኖሪያ ቤት ውስጥ መማሩን እንዲቀጥል ፈለኩኝ። ሃሳቤን መቀየር እችላለሁ?**

ማንኛውም ቤተሰብ፣ በማንኛውም ጊዜ ትምህርት ቤቱን በማነጋገር፣ ወደ መኖሪያ ቤት ተመልሶ ለመማር መቀየር ይችላል። በቤተሰቦች ሁኔታዎች ላይ እና በጤና ሁኔታዎች ላይ ለውጦች ሊኖሩ እንደሚችሉ DCPS ይገነዘባል፤ ስለሆነም፣ ተማሪዎች በማንኛውም ጊዜ ወደ መኖሪያ ቤት ተመልሰው እንዲማሩ ይፈቅድላቸዋል። ተማሪው በአካል ተገኝቶ (in-person) ከመማር ወደ መኖሪያ ቤት ውስጥ መማር ከተዛወረ በኋላ፣ በአሁኑ ተርም (term) ጊዜ ውስጥ እንደገና ወደ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ሊመለስ አይችልም።

**በአካል ተገኝቶ (in-person) መማሪያ ውስጥ ያገኘሁትን ቦታ ካልተቀበልኩ (decline ካደረኩ)፣ ተማሪዬ በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜው ውስጥ ለመካፈል አሁንም ቢሆን ይችላል?**

በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ውስጥ ያገኙትን ቦታ አለመቀበል (Declining ማድረግ) ወይም ቦታዎን ማጣት (losing your seat)፣ በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜው ውስጥ ካለዎት የተጠባባቂነት (waitlist) ቦታ አያስወጣዎትም።

**በአካል ተገኝቶ (in-person) የመማር ክፍለጊዜ የተጠባባቂ ዝርዝሮች እንዴት ነው የሚሰራው?**

ከላይ በተዘረዘረው ቅድሚያ በሚሰጣቸው ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ እና በመጀመሪያ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ውስጥ ቦታ ለማግኘት ያልተዛመዱ፣ በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ይገባሉ። ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ተማሪዎች ጋር፣ የተዛመዱ ተማሪዎች ወንድምና እህታማቾች (siblings)፣ ከተጠባባቂ ዝርዝሩ ከላይ ይሆናሉ። ከወንድምና እህት (siblings)፣ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ በዘፈቀደ (random) የቁጥር አመዳደብ ይቀመጣሉ። ቅድሚያ በሚሰጣቸው ቡድን ውስጥ የሌሉ (Non-priority group) ተማሪዎች፣ በመጨረሻ በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ በዘፈቀደ (random) የቁጥር አመዳደብ ይቀመጣሉ።

ትምህርት ቤቶች በተጠባባቂዎቻቸው ቅደም ተከተል መሠረት ቦታውን ይሰጣሉ። ትምህርት ቤታቸው ውስጥ በልጅዎ የክፍል ደረጃ ቦታ ሲገኝ፣ እና ልጅዎ በተጠባባቂው ዝርዝር ውስጥ ቀጣይ ሆኖ ከተገኘ፣ ትምህርት ቤትዎ በስልክ ያነጋግርዎታል። በምዝገባ ሰነዶችዎ ላይም የኢሜል አድራሻዎን ሰጥተው የሚያውቁ ከሆነም፤ በኢሜልም ማስታወቂያው ይላክልዎታል። ቦታ ከተሰጣችሁ እና በመኖሪያ ቤት ውስጥ መማርን መቀጠል ከመረጣችሁ፣ ቦታውን አለመቀበል (decline ማድረግ) ትችላላችሁ።

**ተማሪዬ በተጠባባቂው ዝርዝር (waitlist) ላይ መኖሩ እና በየትኛው ደረጃ እንደሚገኝ፤ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**

ሁሉም ቤተሰቦች፣ ወይ ይዛመዳሉ ወይም ደግሞ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይሆናሉ። አንዳንድ ቤተሰቦች፣ ተማሪያቸው በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ውስጥ እና በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜ ውስጥም፤ በሁለቱም ውስጥ ተጠባባቂ ሊሆን ይችላሉ። ቤተሰቦችን የምናነጋግራቸው፣ ቦታ ሲሰጣቸው ብቻ ነው። ልጅዎ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ ከፈለጋችሁ፣ እባክዎን በdcps.planning@k12.dc.gov ኢሜል ያድርጉ ወይም ወደ ትምህርት ቤትዎ ይደውሉ።

**ልጄ ከተጠባባቂ ዝርዝሩ (waitlist) ተጠርቶ እንደሆነ እንዴት ይገለጽልኛል?**

ለተማሪዎቻቸው ቦታ ሲገኝላቸው፣ ሁሉም ቤተሰቦች ከትምህርት ቤታቸው በቀጥታ የስልክ ጥሪ እና ኢሜል ያገኛሉ። ትምህርት ቤቱ በተጠባባቂ ዝርዝሩ (waitlist) ቅደም ተከተል መሠረት የስልክ ጥሪዎቹን ያደርጋል። ትምህርት ቤቱ በአሁኑ ጊዜ የሚጠቀሙበት የስልክ ቁጥር እንዳለው እና እንደሌለው እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎን የተስተካከለውን የመገኛ መረጃ ትምህርት ቤቱ እንዲኖረው ይደውሉ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## የተማሪ እንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች

**በትምህርት ቤቱ በእንክብካቤ (CARE) ቦታ ለማግኘት ማን ብቁ ይሆናል?**

እስከ መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም (October 5, 2020) ድረስ የተመዘገቡ ሁሉም ተማሪዎች፣ ቦታ ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ። የDCPS ሠራተኛ ልጆች የሆኑና የተመዘገቡ ተማሪዎች ያሏቸው የተርም (Term) 2ን በአካል ተገኝቶ (in-person) ፕሮግራምን በመጀመሪያ (elementary) ትምህርት ቤት እና የትምህርት ካምፓሶች (education campuses) ውስጥ የሚያግዙ፤ በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ውስጥ ቦታቸው ዋስትና ይገኛሉ።

ከቀሪዎቹ ቦታዎች ውስጥ፣ የመጀመሪያው ተቀዳሚነት የሚሰጣቸው ተማሪዎች፣ ከዕድሉ ባሻገረ ሁኔታ ላይ የሚገኙ የሚከተሉት ቡድኖች (በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማርም ቅድሚያ በመስጠት) እና በወንድምና እህቶቻቸው (siblings) ይሠጣቸዋል። ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት የቡድን አባላቶች ውስጥ የሚገኙ ወንድምና እህታማቾች (siblings)፣ በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ ካልሆኑት ወንድምና እህታማቾች (siblings)፤ በበለጠ ሁኔታ ቅድሚያ ያገኛሉ።

- የቤት-አልባነት (homelessness) የገጠማቸው ተማሪዎች
- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና የግል የትምህርት ዕቅድ (Individualized Educational Plans (IEPs)፣ ያላቸው ተማሪዎች
- በአደጋ ላይ (at-risk) ተብለው የተለዩ ተማሪዎች (ይህ፤ በማደጎ እንክብካቤ ዘዴ ውስጥ ያሉ፣ እና TANF ወይም SNAP ለማግኘት ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን ይጨምራል)።

**ተማሪዬ በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ቦታ ማግኘቱን፣ መቼ እና እንዴት አውቃለሁ?**

ቦታውን ካገኙ፣ ቤተሠቦች ይህንኑ ማስታወቂያ፤ እስከ ጥቅምት 13 (October 30) ድረስ ባለው ጊዜ ኢሜል የሚያገኙ እና ኢሜሉትን ተከትሎ ከትምህርት ቤቱ የስልክ ጥሪ ያገኛሉ።

ውጤቶቹ ከተገለጹ በኋላ፣ ቤተሠቦች ወደ ትምህርት ቤቶቻቸውም መደወል ወይም በdcps.planning@k12.dc.govኢሜል በማድረግ፣ ስለሁኔታቸው ማረጋገጫ ማግኘት ይችላሉ። ማዛመዱ በተከናወነበት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ውስጥ፣ ትምህርት ቤቱ ለሁሉም የተዛመዱ ቤተሰቦች የስልክ ጥሪ ያደርጋል። አንድ ጊዜ ትምህርት ቤቱ ከወላጅ ጋር ከተነጋገረ በኋላ፣ ቦታቸውን ለማረጋገጥ፣ ቤተሰቦች እስከ ሁለት የትምህርት ቀናት ይኖራቸዋል። በዚያ የጊዜ ገደብ ቤተሰቡ ምላሽ ካልሰጠ፣ የተሰጣቸውን ቦታ በማጣት፣ ተማሪዎቻቸው ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) መማርን ይቀጥላሉ። ትምህርት ቤቱ ቤተሰቡን ማግኘት ካልቻለ፣ ምላሽ ባለመስጠጥ ምክንያት ከ5 የትምህርት ቀናት በኋላ ቦታቸው የጊዜ ገደቡ ያልቃል።

**ልጄ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜ ቦታ አግኝቶ ከተዛመደ፣ ቦታውን እንዴት መቀበል እችላለሁ?**

በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜ ቦታ ከተዛመዳችሁ፣ ቦታውን ወዲያውኑ መቀበላችሁን ማሳወቅ አለባችሁ። ቦታውን ለመቀበላችሁ ለማሳወቅ፣ ወደ ትምህርት ቤቱ በመደወልና ቦታውን እንደምትፈልጉት ማረጋገጥን ይጠይቃል። ትምህርት ቤቱ ቤተሰቡን ማግኘት ካልቻለ፣ ምላሽ ባለመስጠጥ ምክንያት ከአምስት የትምህርት ቀናት በኋላ ቦታቸው የጊዜ ገደቡ ያልቃል። በግል የትምህርት ዕቅዳቸው (Individualized Education Plans) ውስጥ፣ ለተማሪው መጓጓዣ አገልግሎት ላላቸው ተማሪዎች፣ ጥያቄውን ለማስገባት እንዲረዳው፣ የትምህርት ቤት ሠራተኛው ስለ መጓጓዣ ፍላጎቶቹ ይጠይቃል።

**ልጄ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜ ቦታ አግኝቶ ከተዛመደ፣ ነገር ግን በመኖሪያ ቤት መማር እንዲቀጥል ከመረጥኩኝ፣ ቦታውን አለመቀበሌን እንዴት ማሳወቅ የምችለው?**

ማንም ቤተሠብ፣ መሳተፍ አያስፈልገውም። ሁሉም ቤተሰቦች፣ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መማርን የመቀጠል አማራጭ አላቸው። በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜ ቦታ ከተዛመዳችሁ፣ እና ቦታውን መቀበል ካልፈለጋችሁ፣ እባክዎን ወዲያውኑ ትምህርት ቤትዎን ደውለው በማነጋገር ያሳውቋቸው፤ (ወይም በdcps.planning@k12.dc.govኢሜል ይድርጉ) ይህን ተከትሎ፣ ትምህርት ቤቱ ቦታውን በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ በሚቀጥለው ቦታ ለሚገኘው ሰው መስጠት ይችላሉ።

**የእንክብካቤ (CARE) ቦታ አግኝቼ ተቀብዬው ነበር፤ ነገር ግን ሃሳቤን ቀይሬ፣ ልጄ ከመኖሪያ ቤት ውስጥ እንዲማር ፈልጌአለሁ። ሃሳቤን መቀየር እችላለሁ?**

ማንኛውም ቤተሰብ፣ በማንኛውም ጊዜ ትምህርት ቤቱን በማነጋገር፣ ወደ መኖሪያ ቤት ተመልሶ ለመማር መቀየር ይችላል። ተማሪው ከእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜ፣ ወደ መኖሪያ ቤት ውስጥ መማር ከተዛወረ በኋላ፣ በአሁኑ ተርም (term) ጊዜ ውስጥ እንደገና ወደ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ወይም በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ለመመለስ አይችሉም።

**እንዴት ነው የተጠባባቂ ዝርዝር (waitlists)፣ በእንክብካቤ (CARE) ቦታዎች ላይ የሚሠራው?**

ከላይ በተዘረዘረው ቅድሚያ በሚሰጣቸው ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ እና በመጀመሪያ ከእንክብካቤ (CARE) ክፍል ውስጥ ቦታ ለማግኘት ያልተዛመዱ፣ በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ይገባሉ። ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ተማሪዎች ጋር፣ የተዛመዱ ተማሪዎች ወንድምና እህታማቾች (siblings)፣ ከተጠባባቂ ዝርዝሩ ከላይ ይሆናሉ። ከወንድምና እህታማቾች (siblings) በኋላ፣ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ በዘፈቀደ (random) የቁጥር አመዳደብ ይቀመጣሉ። ቅድሚያ በሚሰጣቸው ቡድን ውስጥ የሌሉ (Non-priority group) ተማሪዎች፣ በመጨረሻ በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ በዘፈቀደ (random) የቁጥር አመዳደብ ይቀመጣሉ።

ትምህርት ቤቶች በተጠባባቂዎቻቸው ቅደም ተከተል መሠረት ቦታውን ይሰጣሉ። ትምህርት ቤታቸው ውስጥ በልጅዎ የክፍል ደረጃ ቦታ ሲገኝ፣ እና ልጅዎ በተጠባባቂው ዝርዝር ውስጥ ቀጣይ ሆኖ ከተገኘ፣ ትምህርት ቤትዎ በስልክ ያነጋግርዎታል። በምዝገባ ሰነዶችዎ ላይም የኢሜል አድራሻዎን ሰጥተው የሚያውቁ ከሆነም፤ በኢሜል ማስታወቂያው ይላክልዎታል። ቦታ ከተሰጠዎት በኋላ፣ ሙሉ በሙሉ ምናባዊ (all-virtual) ውስጥ መቆየትን ከመረጡ፣ ወደ ትምህርት ቤትዎ በመደወል ወይም በdcps.planning@k12.dc.gov ኢሜል በማድረግ፣ የተሰጠውን ቦታ መውሰድ እንደማይፈልጉ ያሳውቁ።

**ተማሪዬ በተጠባባቂው ዝርዝር (waitlist) ላይ መኖሩ እና በየትኛው ደረጃ እንደሚገኝ፤ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**

ሁሉም የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ ለእንክብካቤ (CARE) ቦታ እና በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር ቦታ ውስጥ፣ በአንደኛቸው፤ ተዛምደው ወይም በተጠባባቂ ዝርዝሩ (waitlist) ይደረጋሉ። ቦታውን የተቀበሉ ቤተሰቦችን ብቻ እናነጋግራቸዋለን። ስለ ተጠባባቂ ዝርዝሩ (waitlist) ምድባቸው፣ ቤተሠቦችን አናሳውቃቸውም። ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎን ወደ ትምህርት ቤትዎ ይደውሉ፣ ወይም በdcps.planning@k12.dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

**ልጄ ከተጠባባቂ ዝርዝሩ (waitlist) ተጠርቶ እንደሆነ እንዴት ይገለጽልኛል?**

ለተማሪዎቻቸው ቦታ ከተገኘላቸው፣ ሁሉም ቤተሰቦች ከትምህርት ቤታቸው በቀጥታ የስልክ ጥሪ እና ኢሜል ያገኛሉ። ትምህርት ቤቱ በተጠባባቂ ዝርዝሩ (waitlist) ቅደም ተከተል መሠረት የስልክ ጥሪዎቹን ያደርጋል።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## ሌሎች ቁልፍ የሆኑ ጥያቄዎች

**መጨረሻ ምዝገባን ካጠናቀኩኝ በኋላ የስልክ ቁጥሬ ወይም የኢሜል አድራሻዬ ተቀይሯል፤ እና አሁን ቦታ ከተሰጠኝ ወይም ተጠባባቂ ቦታ ከተሰጠኝ፣ ትምህርት ቤቱ ሊያገኘኝ የሚችልበት መንገድ የለም ብዬ ሰግቻለሁ። እንዴት ነው የምገኝበትን የአድራሻ መረጃ ማስተካከል (update ማድረግ) የምችለው?**

የተስተካከለውን (updated) የአድራሻ መረጃዎን፣ እባክዎን ከትምህርት ቤትዎ ጋር ያጋሩ።

**ከመስከረም 25 ቀን (October 5) በኋላ ከተመዘገብኩስ፣ ምን ይሆናል?**

እስከ መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም (October 5, 2020) ድረስ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብቻ፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር ወይም በእንክብካቤ (CARE) ክፍለጊዜዎች ውስጥ ለሚደረግ የተማሪ የዘፈቀደ (randomized) የምርጫ ሂደት ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል። ከመስከረም 25 ቀን (October 5) በኋላ ከተመዘገቡ፣ ለተርም (Term) 2 በመኖሪያ ቤት መማር የጊዜ ሰሌዳ ይሰጣችኋል።

**ለDCPS፣ የተማሪ ምርጫ ሂደትን ማን ይቆጣጠርለታል?**

DCPS፣ ተማሪዎችን በብቁነታቸው እና በምጫቸው መመዘኛ መሠረት የሚመድባቸው ስልተ አሰራር (algorithm) መስፈርቶችን ለመቅረጽ፤ ከ'Office of the Chief Technology Officer (OCTO)' ጋር በአጋርነት ይሰራል። OCTO አግባብ ያለው እና ትክክለኛ ሂደትን ለመጠቀም ሲል፣ የ'My School DC' የሚጠቀመውን የሶፍትዌር (software) ፕሮግራም ዘዴን ይጠቀማል። የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ፣ ቦታውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል፤ ከቤተሠቦች ጋር አብረው ይሰራሉ። ተጨማሪ ቦታዎች እየተገኙ ሲመጡ፣ በቤተሰቦች የተጠባባቂ ዝርዝር ቅደም ተከተል መሠረት፤ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ቦታውን መስጠት ይጀምራሉ።

**ስለ ተማሪው የምርጫ ሂደት ጥያቄዎች ካሉኝ፣ ማንን ማነጋገር እችላለሁ?**

ልጅዎ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ ከፈለጋችሁ፣ እባክዎን በdcps.planning@k12.dc.gov ኢሜል ያድርጉ ወይም ወደ ትምህርት ቤትዎ ይደውሉ። ለአጠቃላይ ጥያቄዎችዎ፣ እባክዎን በdcps.planning@k12.dc.gov ኢሜል አድርጉልን።